# በግፍ የተፈረደባቸዉን የቅንጅት አመራር አባላት አስመልክቶ ከትብብር ለነፃነትና ዲሞክራሲ (ትነዲ) የተሰጠ መግለጫ

ሰኔ 14 1999 ዓም

ባለፉት 16 ዐመታት የኢትዮጵያ ሕዝብ በከፋ የወያኔ አምባገነናዊ አገዛዝ ስር መከራዉን ሲያይ ኖሯል:: ሰፋፊ የሰባዊ መብት ረገጣዎች፣ የህጋዊ ስነስርአት እና ደንብ ፍፁም የሚፃረሩ ጥሰቶች፣ እንዲሁም መሰረታዊ የሆኑ የዲሞክራሲ መብቶች አለመኖራቸዉ፣ በተለየም የፍትህ ስርዓቱ ከስራ አስፈፃሚዉ አካል ቀጥተኛ ጣልቃገብነት ነፃ አለመሆን በተለያዩ አለም አቀፍ የሰባዊ መብት ተሚጋች ድርጅቶች በሚገባ ተመዝግቧል:: ይህዉም አሳዛኝ ገሃድ የወጣ ሀቅ ስለ ነፃነት መብትና ዲሞክራሲ እየለፈለፉ በሃገሬዉ ህዝብ በሙሉ የተተፋዉን መንግስት ነፍስ እየዘሩለት ካሉት ታላላቅ ምዕራባዊያን መንግስታት የተሰወረ አይደለም:: ወያኔ በመላዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተተፍቶ ራቁቱን ከቀረበት የግንቦት 97 ምርጫ ወዲህ ሁኔታዎች በፍጥነት እየተባባሱ መጥተዋል:: ወያኔ ግን ከሕዝቡ ፍላጎት ዉጪ በጠመንጃዉ ተማምኖ ስልጣኑን የሙጥኝ ብሏል::

ትብብር ለነፃነትና ዲሞክራሲ (ትነዲ) በቅንጅት አመራር የፈጠራ ክስ ላይ የተሰጠዉን ኢፍትሃዊ ብይን ኣጥብቆ ያወግዛል:: ይኽ ለፖለቲካ ጠቀሜታ ሲባል አመኔታ ቢስ በሆነው ካንጋሩ ፍርድ ቤት የተወሰደ ድንገተኛ እና ሕገወጥ ዉሳኔ የሚያሳየዉ የኢሕኣዴግን ኣምባገነናዊነትና ተስፋ መቁረጥ ነዉ::

በተጨማሪም ሰሞኑን በኦጋዴን እየተካሄደ ያለዉ በሰላማዊ ሕዝብ ላይ ያነጣጠረዉ የከፋት አፈና እርምጃ፣ በኦሮሚያ፣ በሲዳማና በኣማራ ክልሎች የተማሪዎች ኣስተማሪዎችና ሙያተኞች እስራት እንዲሁም በወያኔ አነሳሽነት በሃገሪቱ የነገሰዉ አጠቃላይ ሽብር የሚያሳስብና ሊፈነዳ የሚችል የፖለቲካ ዉጥረት ፈጥሯል::

እንደ ትብብሩ እምነት የሚያዋጣዉ፣ ተጨማሪ የመብት ረገጣ ወይም በህግ ሽፋን ሌላ የፍትህ ማጣመም ማካሄድ ሳይሆን ሃገሪቷን ወደ ፍትሃዊ፣ ሰፊ ተዋፅኦ ያለዉና ዲሞክራታዊ ስርአት በሰላም የሚያሸጋግር ሁሉን አቀፍ የሆነ አገራዊ ጉባኤ ማሰባሰብ ነዉ:: ከዚህ በፊት በየኢትዮጵያ ላሉት ቅራኔዎች በሰላማዊ መንገድ እልባት ለማስገኘት የተደረጉ አያሌ  የዕርቅ ጥረቶች በወያኔ እምቢተኝነት ዋጋቢስና ከንቱ ልፋት ሆነዉ መቅረታቸዉ ይታወቃል:: ዛሬ ግን የቁርጥ ቀን የደረስ ስለሆነ ወያኔ ከጥፋት መስመሩ በመታቀብ ወደ ህሊናዉ መመለስ የሚሳነዉ ከሆነ ለሚደርሰዉ ጥፋት ብቸኛ ተጠያቂ መሆኑን ትብብሩ ከወዲሁ ያስጠነቅቃል::

የአለም ኣቀፍ ማህበረሰብ በወያኔ ላይ ጫና በማድረግ የቅንጅት አመራረና ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ባሰቸኳይ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱና ሰላምና  ዕርቅን በዉይይትና በድርድር ለማስገኘት የተሰነዘረዉን ጥሪ በቀና እንዲቀበል በወያኔ ላይ ጫና እንዲያደርጉ እንጠይቃለን:: ወያኔን ለአምባገነን ተግባሩ ተጠያቂ የማድረግ ቀዳሚ ሃላፊነት የኢትዮጵያ ህዝብ ቢሆንም በሥልጣን ላይ እንዲቆይ እያደረጉ ያሉ ደጋፊዎቹ ህዝቡ ካሁን በኋላ በጠመንጃ አፈሙዝ እንኳን በጭቆና ሥር ፀጥ ብሎ የመኖር ትዕግስቱ የተሟጠጠ መሆኑን መገንዘብ ኣለባቸዉ::

በዚህ ኣስቸጋሪና ፈታኝ ቀዉጢ ወቅት የትብብሩ አባላት ኢፍትሃዊ ፍርድ ከተፈረደባቸዉ የቅንጅት መሪዎች፣ በተለያዩ እሥር ቤቶችና ሚስጥራዊ የመያዣ ካምፖች ታጉረዉ ከሚጎሳቆሉ ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ጋር እንደሚወግንና ለቤተሰቦቻቸዉም ያላቸዉን ጥብቅ ሃዘን ይገልፃሉ::

የኢትዮጵያ ህዝብ ለነፃነትና ዲሞክራሲ የሚያደርገዉ ትግል ያሸንፋል!
ትብብር ለነፃነትና ዲሞክራሲ (ትነዲ)